*<u>በጥቅማ ጥቅሞች ላይ ሊኖር የሚችል</u>*

*መረጃ ብቻ*

**መግቢያ:** ይህ መረጃ Fairfax County Economic Mobility Pilot (ከፌርፋክስ ካውንቲ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ምኮራ) የሚገኘው ወርሃዊ ክፍያ እንዴት ህዝባዊ ጥቅማጥቅሞችን ተጽዕኖ እንደሚያደርግ ግለሰቦችን እንዲረዱት ለመርዳት የተነደፈ ነው።

ጥቅማጥቅሞቹ ተጽእኖ ሊደርስባቸው የሚችልበት ሶስት ዋና መንገዶች አሉ፥

- ***ምንም የሚታወቅ ተፅዕኖ የለም: ፓይለቱ ከተጀመረ ጀምሮ፣*** ወርሃዊ ክፍያዎችን በመቀበልዎ በብቁነትዎ ወይም የጥቅማጥቅሞችዎ መጠን ላይ ምንም የሚታወቅ ተፅዕኖ የለም።
- ***ሊያጋጥሙ የሚችሉ የጥቅማ ጥቅሞች መቀነስ:*** ወርሃዊ ክፍያዎችን *መቀበል* የጥቅማጥቅሞችን መቀነስ ሊያስከትል ይችላል፣ ይህ ማለት አሁንም ጥቅሙን ሊያገኙ ይችላሉ፣ ግን በየወሩ እየቀነሰ የሚሄድ ሊሆን ይችላል።
- ***ሊከሰቱ የሚችሉ ጥቅሞችን ማጣት:*** ከ FCEMP ክፍያዎች ውጭ በሚያገኙት ገቢ ላይ በመመስረት፣ ወርሃዊ ክፍያዎችን *መቀበል* ጥቅማ ጥቅሞችን ሊያሳጣ ይችላል

***ማሳሰቢያ፡ ይህ ለአጠቃላይ መረጃ ብቻ ነው። የእያንዳንዱ አመልካች ሁኔታ በጥንቃቄ ሊታሰብበት ይገባል እና ጥቅሞቻቸውን ለሚያስተዳድረው ኤጀንሲ እንደ አስፈላጊነቱ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለባቸው።***

| ህዝባዊ ጥቅማ ጥቅም | ይህ ምንድነው? | የሚጠበቀው ተፅዕኖ |
|---|---|---|
| የፌዴራል ተጨማሪ ደኅንነት ገቢ (SSI) | ለአዋቂዎች እና ለአካል ጉዳተኞች ዝቅተኛው መሰረታዊ የገንዘብ ድጋፍ | **ሊፈጠር የሚችል የጥቅማ ጥቅም ማጣት**<br>የ SSI የገቢ ገደቦች እና ደንቦች ውስብስብ ናቸው። በ ሙከራ ውስጥ መሳፍቻ የሚያገኙት ክፍያዎች ከ ግምት **ውስጥ** የሚገቡ ሲሆን ለ SSI ብቁ እንዳይሆኑ ሊያደርጓቸው ይችላሉ። |
| ሜዲኪይድ (የጤና መድን) | ለህፃናት እና ለአዋቂዎች ነፃ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያለው የጤና መድን። | **ሊያጋጥም የሚችል የጥቅማ ጥቅም ማጣት** በ ሙከራ ውስጥ በመሳተፍ የሚቀበሉት ክፍያዎች እንደ ሳይሰሩ የተገኙ ገቢዎች **ሊቆጠሩ** ይችላሉ እና ከብቁነት ጋር እንደሚቃረናሉ ይታሰባሉ።<br>የእርስዎ ቤተሰብ አስቀድሞ ምን ያህል ገቢ እንደሚያገኝ ላይ በመመስረት |

FAIRFAX COUNTY ECONOMIC MOBILITY PILOT

*በጥቅማ ጥቅሞች ላይ ሊኖር የሚችል*

*መረጃ ብቻ*

| ህዝባዊ ጥቅማ ጥቅም | ይህ ምንድነው? | የሚጠበቀው ተፅዕኖ |
|---|---|---|
| | | ከ ምኮራው የተቀበሉት የገንዘብ ድጎማ ከገቢ ገደቦች በላይ በመሆናቸው ለMedicaid (የጤና መድን) ብቁ እንዳትሆኑ ሊያደርግ ይችላል። |
| ተጨማሪ የአመጋገብ እርዳታ ፕሮግራም (SNAP) የምግብ እርዳታ | ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ጎልማሶች እና ቤተሰቦች ብቁ የሆኑ ምግቦችን በተፈቀደላቸው የችርቻሮ ምግብ መደብሮች ለመግዛት የምግብ እርዳታ። | **ሊፈጠር የሚችል የጥቅማ ጥቅም ቅነሳ /ማጣት**<br>በፓይለቱ ውስጥ በመሳተፍ የሚያገኙት **ክፍያዎች** ለ SNAP ብቁነት ይቆጠራሉ። የእርስዎ ቤተሰብ አስቀድሞ ምን ያህል ገቢ እንደሚያገኝ ላይ በመመስረት፣ ከ ምኮራው የተቀበሉት የገንዘብ ድጎማ ከገቢ ገደብ በላይ በመሆናቸው ለ SNAP ብቁ እንዳትሆኑ ያደርጋችኋል ወይም የ SNAP ጥቅማ ጥቅሞችን መጠን ይቀንሳል። |
| የሕዝባዊ መኖሪያ ቤት (ክፍል 8) እና የቤቶች ምርጫ ሰነዶች | በመንግስት ባለቤትነት በተያዘው መኖሪያ ቤት ወይም በሰነዶች በግል ገበያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች የመኖሪያ ቤት ድጋፍ። | **በጥቅማ ጥቅም ላይ ሊፈጠር የሚችል ቅነሳ /ማጣት**<br>በምኮራው ውስጥ በመሳተፍ የሚያገኙት **ክፍያዎች** ለቤት እርዳታ እንደ ገቢ ይቆጠራል። |
| ፔል ግራንት | የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (ኮሌጅ፣ ተባባሪ ዲግሪ) የገንዘብ እርዳታ። | **ሊፈጠር የሚችል የጥቅማ ጥቅም ቅነሳ**<br>የገንዘብ ዕርዳታው መጠን ከሁለት ዓመት በፊት ባገኘኸው ገቢ መሰረት ይሰላል። እርስዎ ወይም ጥገኞች ከሁለት አመት በኋላ ኮሌጅ ለመግባት ከወሰኑ፣ ከምኮራው በሚቀበሉት ክፍያ ላይ ተመስርቶ መጠኑ ሊቀንስ ይችላል። |
| ሴቶች፣ ጨቅላዎች እና ህፃናት (WIC) | ተጨማሪ ምግቦች፣ የጤና ክብካቤ ሪፈራሎች እና የአመጋገብ ትምህርት ለእናቶች፣ እና እስከ አምስት አመት እድሜ ያላቸው በአመጋገብ አደጋ ላይ | **ሊፈጠር የሚችል የጥቅማ ጥቅም ማጣት**<br>ለWIC ብቁ መሆንን ሲወስኑ ከምኮራው **የሚቀበሉት** ክፍያ በግምት ውስጥ ይገባል። |

የፌርፋክስ ካውንቲ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ምኮራ 2023

ማሳሰቢያ፡ ይህ ለአጠቃላይ መረጃ ብቻ ነው። የእያንዳንዱ አመልካች ሁኔታ በጥንቃቄ ሊታሰብበት ይገባል እና ጥቅሞቻቸውን ለሚያስተዳድረው ኤጀንሲ እንደ አስፈላጊነቱ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለባቸው።

FAIRFAX COUNTY ECONOMIC MOBILITY PILOT

***በጥቅማ ጥቅሞች ላይ ሊኖር የሚችል***

***መረጃ ብቻ***

| **ህዝባዊ ጥቅማ ጥቅም** | **ይህ ምንድነው?** | **የሚጠበቀው ተፅዕኖ** |
|---|---|---|
| | ላሉ ህጻናት እና ጨቅላዎች። | |
| ነፃ እና የተቀነሰ ዋጋ ያለው የትምህርት ቤት ምሳ | በሕዝባዊ ትምህርት ቤቶች ለተመዘገቡ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ልጆች ነፃ ወይም በአነስተኛ ወጪ የትምህርት ቤት ምሳዎች። | **ሊፈጠር የሚችል የጥቅማ ጥቅም ቅነሳ /ማጣት**<br>ብቁነት በዓመት አንድ ጊዜ የሚወሰን ሲሆን **ከፓምኮራው** የሚከፈለው ክፍያ በብቁነት ላይ ይቆጠራል። በሚቀጥለው ጊዜ ብቁነት ሲገመገም (ምናልባት በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ የሚሆን) ይህ ፕሮግራም ከነጻ ወደ ዋጋ ወደተቀነሰ ምግብ ሊያንቀሳቅስ ወይም ብቁ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል። |
| ሜዲኬር (የጤና መድን) | ነፃ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያለው የጤና መድን ለአረጋውያን። | **ሊፈጠር የሚችል የጥቅማ ጥቅም ቅነሳ**<br>ከምኮራው የሚቀበሉት **ክፍያዎች** ለሜዲኬር (የጤና መድን) ክፍል B (ኢንሹራንስ) እና D (በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶች) ወጪዎች ብቁነት ላይ ይቆጠራሉ። የጥሬ ገንዘብ ክፍያው ለሜዲኬር (የጤና መድን) ክፍል B ፕሪሚየም መክፈል ያለብዎትን መጠን ሊጨምር እና በሜዲኬር (የጤና መድን) ክፍል D ስር ለመድኃኒቶች ከኪስዎ<br>የሚወጣውን ወጪ ሊጨምር ይችላል። |
| TANF | መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለመደገፍ ጊዜያዊ የገንዘብ ድጋፍ። | **ምንም የሚታወቅ ተፅዕኖ የለም።**<br>ለ TANF ብቁ መሆንን በሚወስኑበት ጊዜ በምኮራው **ውስጥ** በመሳተፍ የሚቀበሉት ክፍያ እንደ ገቢ አይቆጠርም። |
| የሕፃናት እንክብካቤ እርዳታ | የህጻን እንክብካቤ ድጎማዎች (በተጨማሪም ሰነዶች እና የክፍያ እርዳታ ተብለው ይጠራሉ) | **ምንም የሚታወቅ ተፅዕኖ የለም።**<br>በምኮራው ውስጥ በመሳተፍ የሚያገኙት<br>**ክፍያዎች** ለ SNAP ብቁነት በሚወሰንበት ግዜ እንደ ገቢ ኣይቆጠርም። |

FAIRFAX COUNTY ECONOMIC MOBILITY PILOT

*በጥቅማ ጥቅሞች ላይ ሊኖር የሚችል*

*መረጃ ብቻ*

| **ህዝባዊ ጥቅማ ጥቅም** | **ይህ ምንድነው?** | **የሚጠበቀው ተፅዕኖ** |
|---|---|---|
| ማህበራዊ ደኅንነት (ጡረታ) | የጡረታ ገቢ ቢያንስ 61 ዓመት ከ 9 ወር ለሆኑ አዋቂዎች የሚከፈል። | **ምንም የሚታወቅ ተፅዕኖ የለም።**<br>ብቁነት ለማህበራዊ ደህንነት በቀደሙት አስተዋጾ በነበራቸው ላይ የተመሰረተ ነው። በምኮራው ውስጥ በመሳተፍ የሚያገኙት **ክፍያዎች የእርስዎ ማህበራዊ** ደህንነት የጡረታ ክፍያዎች ላይ ተጽዕኖ አይኖራቸውም። |
| የማህበራዊ ደህንነት የአካል ጉዳት መድን (SSDI) | የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ እና ብቁ የሆነ የሥራ ታሪክ ላላቸው ግለሰቦች፣ በራሳቸው ሥራ ወይም በቤተሰብ አባል<br>የገንዘብ ድጋፍ። | **ምንም የሚታወቅ ተፅዕኖ የለም።**<br>ብቁነት በቀደሙት አስተዋጾ ለማህበራዊ ድሕንነት እና መስራት በአለመቻል ላይ የተመሰረተ ነው። የ SSDI ብቁነት ወይም **መጠን** ሲወስኑ በምኮራው ውስጥ በመሳተፍ የሚያገኙት ክፍያዎች ግምት ውስጥ አይገቡም። *ነገር ግን፣ ከቅጥር ስራ የሚገኘው ገቢ በጥቅማጥቅሞችን ተጽዕኖ ሊያደርግ ይችላል።* |
| የሥራ አጥነት መድን (UI) | አዲስ ሥራ በሚፈልጉበት ጊዜ ወጪዎችን ለማሟላት እንዲረዳቸው ሥራቸውን ለሚያጡ አዋቂዎች<br>ጊዜያዊ እርዳታ። | **ምንም የሚታወቅ ተፅዕኖ የለም።**<br>በምኮራው ውስጥ በመሳተፍ የሚያገኙት<br>**ክፍያዎች የኮቪድ** እርዳታ ስለሚቆጠር ለብቁነት አይቆጠሩም። |

**ለተጨማሪ ጥያቄዎች እባክዎትን ጥቅማ ጥቅሙን የሚሰጠውን ኤጀንሲ ያነጋግሩ።**

ስለ SSDI ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የግልዎ ሁኔታዎን ለመገምገም የነጻነት ማእከልን ያነጋግሩ።


ማሳሰቢያ፡ ይህ ለአጠቃላይ መረጃ ብቻ ነው። የእያንዳንዱ አመልካች ሁኔታ በጥንቃቄ ሊታሰብበት ይገባል እና ጥቅሞቻቸውን ለሚያስተዳድረው ኤጀንሲ እንደ አስፈላጊነቱ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለባቸው።